


# ሴኔት

– በጥንቷ፡ ሮም፡ ታሪክ፡ ውስጥ፡ ትልቅ፡ የፖለቲካ፡ አካል፡ (ተቋም)፡ ነበር። ሴኔቱ፡ አሉ፡ የሚባሉ፡ እና፡ ሀብታም፡ ከሆኑ፡ ወንድች፡ የተውጣጣ፡ ስብስብ፡ ነበር።

– የሴኔቱ፡ ሚና፡ ከጊዜ፡ በኋላ፡ ተለውጧል።፡ በመጀመሪያዎቹ፡ ዓመታት፣ የሮም፡ ሴኔት፡ ንጉሱን፡ ማማከር፡ ላይ፡ ነበር፡ የሚሰሩት።፡ ነገርግን፡ በሮም፡ ሪፐብሊክ፡ ዘመን፡ ሴኔቱ፡ ይበልጥ፡ ጠንካራ፡ ሆነ።፡ ምንም፡ እንኳን፡ ሴኔቱ፡ ህጎችን፡ ባያወጣም፡ ደንቦችን፡ ያረቁ፡ ነበር።፡ የሚወጡት፡ ደንቦቹም፡ በአጠቃላይ፡ ተፈፃሚ፡ ነበሩ።፡ በተጨማሪ፡ ሴኔቱ፡ የመንግስትን፡ ገንዘብ፡ ስለሚቆጣጠሩ፣ በጣም፡ ጠንካራ፡ አድርጓቸዋል።፡ በኋላም፣ ሮም፡ በንጉሳዊያን፡ ዘመን፡ መገዛት፡ ስትጀምር፡ ሴኔቱ፡ ያነሰ፡ ኃይል፡ ነበረው። እውነተኛው፡ ስልጣንም፡ በንጉሠ፡ ነገሥታት፡ ተያዘ።

– ከአሜሪካ፡ ሴናተሮች፡ በተቃራኒ፡ የሮም፡ ሴናተሮች፡ ተመርጠው፡ ሳይሆን፡ ተሹመው፡ ነው፡ ስልጣን፡ የሚዪዙት።፡ በሮም፡ ሪፐብሊክ፡ አንድ፡ ተመራጭ፡ ባለስልጣናት፡ ወይም፡ ቆንሲሎች፡ [Consuls]፡ አዲስ፡ ሴናተሮችን፡ ይሾሙ፡ ነበር።፡ በኃላ፡ ግን፡ በንጉሳዊያን፡ ዘመን፡ ንጉሱ፡ ነበር፡ የሚሾመው።

– በሮም፡ የመጀመሪያ፡ ታሪክ፡ ውስጥ፡ ከፓትሽያን፡ [Patrician]፡ ክፍል፡ የሆኑት፡ ወንዶች፡ ብቻ፡ ነበሩ፡ ሴናተር፡ መሆን፡ የሚችሉት።፡ በኃላ፡ ግን፡ ከተራው፡ ክፍል፡ ወይም፡ [Plebeians]፡ ወንዶች፡ ሴናተር፡ መሆን፡ ቻሉ።፡ በንጉሠ፡ ነገሥት፡ በአጎስተስ፡ [Augustus]፡ የግዛት፡ ዘመን፡ ሴናተሮች፡ ከ1፡ ሚሊዮን፡ በላይ፡ ሴስተረስ፡ [Sesterces]፡ [የጥንታዊ፡ የሮማውያን፡ ሳንቲም]፡ እንዲኖራቸው፡ ይጠበቅባቸው፡ ነበር።፡ ይህንን፡ የሀበት፡ መጠን፡ በክፉ፡ አጋጣሚ፡ ሀብታቸውን፡ ካጡ፡ ሥልጣናቸውን፡ መልቀቅ፡ ይጠበቅባቸው፡ ነበር።

## በቁጥር፡ ስንት፡ ሴናተሮች፡ ነበሩ?

– በሮማን፡ ሪፐብሊክ፡ ውስጥ፡ 300፡ ሴናተሮች፡ ነበሩ።፡ ይህ፡ ቁጥር፡ ወደ፡ 600፡ ከፍ፡ ብሎ፡ ነበር። ከዚያም፡ በጁሊየስ፡ ሴዛር፡ [Julius፡ Caesar]፡ ዘመን፡ 900፡ ደረሱ።

## የአንድ፡ ሴናተር፡ መስፈርቶች

– ሴናተሮች፡ ከፍተኛ፡ ሥነ፡ ምግባር፡ እንዲኖራቸው፡ ይጠበቅባቸው፡ ነበር።፡ ለሚሰሩት፡ ስራ፡ ስለማይከፈላቸው፡ ሀብታም፡ መሆን፡ እና፡ ሀብታቸውን፡ ለሮም፡ መንግሥት፡ በመርዳት፡ እንዲያውሉ፡ ይጠበቅባቸው፡ ነበር።፡ እንዲሁም፡ ባለ፡ ባንክ፡ እንዲሆኑ፣ በውጭ፡ ንግድ፡ ውስጥ፡ ተሳትፎ፡ እንዳይኖራቸው፡ እና፡ ወንጀል፡ መፈፀም፡ አይፈቀድላቸውም፡ ነበር።

## ሴናተሮች፡ ልዩ፡ መብቶች፡ ነበሯቸው?

– ምንም፡ እንኳን፡ ሴናተሮች፡ ደመወዝ፡ ባይከፈላቸውም፣፡ በሴኔቱ፡ ውስጥ፡ አባል፡ መሆን፡ የሮም፡ ሰዎች፡ የዕድሜ፡ ልክ፡ ግብ፡ ነበር።፡ የሴኔት፡ አባል፡ መሆን፡ በመላው፡ ሮም፡ ታላቅ፡ ዝናን፡ እና፡ ክብር፡ ያስገኝ፡ ነበር።፡ ሴናተሮች፡ ብቻ፡ ነበሩ፡ ሐምራዊ፡ ቀለም፡ ያለው፡ ቀሚስ፡ እና፡ ልዩ፡ ጫማዎች፡ የሚለብሱት።፡ እንዲሁም፡ በሕዝባዊ፡ ዝግጅቶች፡ ላይ፡ ልዩ፡ መቀመጫዎች፡ የሚያገኙ፡ ሲሆን፡ ከፍተኛ፡ ማዕረግ፡ ያላቸው፡ ዳኞች፡ ሊሆኑ፡ ይችላሉ።

## ደንቦችን፧ ማውጣት

– ሴኔቱ፧ በወቅታዊ፧ ጉዳዮች፧ ላይ፧ ለመወያየት፧ ይሰበሰቡ፧ ነበር።፧ ከዚያም፧ ለቆንስል፧ [Consuls]፧ ደንቦችን፧ እና፧ ምክሮችን፧ ያወጣሉ።፧ ውሳኔ፧ ከመስጠታቸው፧ በፊት፧ እያንዳንዱ፧ ተሰብሳቢ፧ ለጉዳዩ፧ እንደ፧ ቅደም፧ ተከተላቸው፧ ይናገራል።

## እንዴት፧ ነው፧ ድምጽ፧ የሚሰጡት?

– እያንዳንዱ፧ ሴኔት፧ በአንድ፧ ጉዳይ፧ ላይ፧ የመናገር፧ እድል፧ ካገኘ፧ በኋላ፧ ድምጽ፧ ይሰጥበት፧ ነበር።፧ በአንዳንድ፧ ሁኔታዎች፧ የሴኔቱ፧ አባላት፧ ወደ፧ ተናጋሪው፧ ወገን፧ ወይም፧ ወደ፧ ተሰብሳቢዎች፧ ድጋፍ፧ ይሰጡ፧ ነበር። በብዛት፧ የሴኔቱ፧ አባላት፧ የሰጡት፧ ድምፅ፧ አሸናፊ፧ ይሆናል።

## ስለ፧ ሮማን፧ ሴኔት፧ አስገራሚ፧ እውነታዎች

– የሮማውያን፧ ሴናተሮች፧ የህይወት፧ ዘመን፧ ሹመት፧ ነው፧ የሚያገኙት።፧ በሙስና፧ ወይም፧ በተወሰኑ፧ ወንጀሎች፧ ሊወገዱ፧ ይችላሉ።

– አንድ፧ ሴናተር፧ ከሴኔት፧ ፈቃድ፧ ካልተቀበለ፧ በስተቀር፧ ከጣልያን፧ (ከሮም)፧ ለቆ፧ መሄድ፧ አይፈቀድለትም፧ ነበር።

– በችግር፧ ጊዜ፧ ሴኔቱ፧ ሮምን፧ እንዲመራ፧ አንባገነን፧ መሪ፧ ሊሾሙ፧ ይችላሉ።

– ሴኔቱ፧ የሚሰበሰብበት፧ ህንጻ፧ ኩርያ፧ [Curia]፧ ይባላል።

– በሮም ግዛት ውስጥ ንጉሠ ነገሥቱ ብዙውን ጊዜ የሴኔቱን በላይነት ይቆጣጠሩ ነበር። ንጉሱ ሁለቱ ቆንስላዎች መካከል ተቀምጦ በፈለገው ጊዜ መናገር ይችል ነበር።

@nebeb_ethiopia, ንበብ፧ ኢትዮጵያ